## ለመመረቅ መቃረብ

# 2028 ተመራቂዎች

### ዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያ ዓመት:- 2024–2025

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመመረቂያ መስፈርቶች በአጭሩ

**የሜሪላንድ ስቴት 1 ዲፕሎማ የሚሰጠው**ለሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምሩቃን ሲሆን፣ ይኼውም አራት መስፈርቶችን በተሳካ ሁኔታ በማሟላት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም:- ምዝገባ፣ የኮርስ ክሬዲት፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) እና የሜሪላንድ መመዘኛዎችን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ናቸው። ተማሪዎች የመመዝገቢያ መስፈርቱን ለማሟላት ከ 8ኛ ክፍል በኋላ የአራት አመት ትምህርታቸውን በተገቢ መንገድ ማጠናቀቅ አለባቸው።ይሄ የማያስፈልግ ከሆነ አማራጭ የምዝገባ ዕቅድ ተዘጋጅቶ "ደንብ ISB-RA" ላይ በተገለፀው መሰረት ገደቡ እንዲነሳ ከተፈቀደ ብቻ ነው። ሌሎች ተፈላጊ መስፈርቶች በሙሉ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ባጭሩ ተገልፀዋል። እባክዎ ስለ 2022–2023 ኦንላይን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የኮርስ መፅሔት (Bulletin) በዚህ ድረገጽ ላይ ይመልከቱ:- coursebulletin.montgomeryschoolsmd.org/Home/PlanningTools ወይም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የእርስዎን ትምህርት ቤት ካውንስለር ያነጋግሩ።

## የኮርስ ክሬዲቶች

| | |
|---|---|
| የኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኢንጅነሪንግ ወይም የቴክኖሎጅ ትምህርት (TE) | 1 ክሬዲት ለ..የተመደበTE። ይሄንን መስፈርት የሚያሟሉ ኮርሶች የሚገኙት በኮርስ መግለጫ መጽሔት ውስጥ ሲሆን የሚያካትተውም የኮምፒውተር እና የአልጎሪዝሚክ (algorithmic) ትምህርት ወይም ችግሮችን የመፍታት እና የሰው ልጅ እምቅ ችሎታዎች የእውቀት፣ የመገልገያ መሳሪያዎች፣ እና የክህሎት ትግበራን ነው። |
| እንግሊዘኛ | 4 ክሬዲቶች በሥነ ጽሑፍ እና በመረጃ አቀራረብ፣ መጻፍ፣ ንግግር እና ማዳመጥ፣ቋንቋ እና ንባብን በተደራጀ መልኩ መማር፣ ከእነዚህ ውስጥ 1 ክሬዲት ከሜሪላንድ አጠቃላይ (MCA) የእንግሊዝኛ ምዘና ጋር የተሳለጠ መሆን አለበት። |
| ስነ ጥበብ | 1 ክሬዲት ዳንስ፣ የሚድያ አርት፣ ሙዚቃ፣ ቲያትር፣ ወይም ቪዡዋል አርት፣ ወይም እነዚህን በማጣመር። |
| የጤና ጥበቃ ትምህርት | 1 ክሬዲት፣ ኦነርስ የጤና ትምህርት A/B |
| ሂሳብ | 4 ክሬዲቶች ፣ በአልጀብራ ትምህርት 1 የሚያካትተው MCA በአልጀብራ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር መጣጣም አለበት ወይም 1 ወይም ከዚያ በላይ ክሬዲቶች በተከታታይ በሚወሰድ የሂሳብ ኮርሶች አልጀብራ 1 እንደ ቅድመሁኔታ መሟላት አለበት፣ እና ከጂኦሜትሪ 1 ይዘት ጋር የሚሠላ ነው።<br>በ 2018 እና ከዚያ በኋላ ለሚመረቁ ተማሪዎች የስቴት መስፈርቶች። በ 2018 እና ከዚያ በኋላ የሚመረቁ ተማሪዎች በያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዓመት የሂሳብ ኮርስ መውሰድ አለባቸው። ይህ ለተማሪዎች መመረቂያ በሂሳብ ከ 4 ክሬዲቶች በላይ ሊያስገኝላቸው ይችላል። |
| የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት | 1 ክሬዲት |
| ሳይንስ | 3 ክሬዲቶች ደረጃውን የጠበቀ የቀጣይ ትውልድ ሳይንስ/ Next Generation Science Standards (NGSS)፣ በስነ ህይወት ሳይንስ የሜሪላንድ የተቀናጀ ሳይንስ ምዘና (MISA) ጋር የተሣለጠ 1 የስነ ህይወት ሳይንስ ክሬዲት፣1 ፊዚካል ሳይንስ ክሬዲት፣ እና 1 ክሬዲት በየብስ/መሬት/የጠፈር ሳይንስ ወይም NGSS ኮርስ ጋር የተቀናጀ የብስ/የምድር/የጠፈር ሳይንስ ኮርስ። |
| የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ | 3 ክሬዲቶች፣ 1 ክሬዲት ዩ.ኤስ ታሪክ፣ 1 ክሬዲት የአለም ታሪክ፣ እና 1 ናሽናል፣ ስቴት፣ እና MCA ስነ መንግስት ከሚሰጠው ትምህርት ጋር የተቀናጀ የአካባቢ ስነ-መንግስት ክሬዲት መሆን አለበት። |
| የአለም ቋንቋዎች ትምህርት እና በምርጫ የሚወሰድ (ELECTIVES) ፕሮግራም | 2 ክሬዲቶች በተመሳሳይ የአለም ቋንቋ መገኘት ያለበት ሲሆን ይሄውም 2 ክሬዲቶች በአሜሪካ የምልክት ቋንቋ ወይም 2 ክሬዲቶች በምርጫ የሚወሰዱ (elective) ኮርሶች መሆን አለበት፣<br>**ወይም**<br>በስቴት የጸደቀ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (CTE) ፕሮግራም (POS) ማጠናቀቅ እናቢያንስ 0.5 ክሬዲት POS ላይ በመመስረት በተመረጡ ኮርሶች ወይም ከዚያ በላይ የተገኘ። |

## የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)

| | |
|---|---|
| የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) | 75 የአገልግሎት-ትምህርት ሰአቶች<br>ከ 6ኛ ክፍል በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ MCPS ለሚገቡ ተማሪዎች SSL መስፈርት በተመዛዛኝ ይያዛል። |

## የሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘና (MCA) መስፈርቶች[1፣2]
## እነዚህ የምዘና መስፈርቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) አማካይነት ሊለወጡ ይችላል።

| | |
|---|---|
| አልጀብራ 1 | በአልጀብራ 1 የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• የአልጀብራ 1 ምዘና/ፈተና መውሰድ<br>• በ 2019-2020 የአልጀብራ 1 ኮርስ ያለፈ(ች) ከሆነ፣ ማሟላት የሚጠበቅበ(ባ)ት የኮቪድ ምርመራ መስፈርት እንዲቀር ይደረጋል። ምንም ተጨማሪ የምርመራ ተሳትፎ ማድረግ አያስፈልግም፥ ስለሆነም የተማሪው(ዋ) ምርመራ "አስፈላጊ አይደለም" ተብሎ ይመዘገባል። |
| እንግሊዝኛ 10 | እንግሊዝኛ 10 ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት፣ ወይም እንግሊዝኛ 10 ELs የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ ፈተና (ምዘና) መውሰድ |
| ስነ መንግስት | ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት እና<br>• B ሴሚስተር የኮርስ መጨረሻ ላይ የስነ መንግስትን ምዘና መውሰድ። የፈተና ውጤቱ የመጨረሻው ሴሚስተር B ኮርስ ውጤት ላይ 20% ይቆጠራል። |
| ሳይንስ | በባዮሎጂ ወይም በሌላ ተመጣጣኝ ኮርስ የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• B ሴሚስተር ኮርስ መጨረሻ ላይ የስነ ህይወት ሳይንስ ምዘና መውሰድ። የፈተና ውጤቱ የመጨረሻው ሴሚስተር B ኮርስ ውጤት ላይ 20% ይቆጠራል። |

[1]የማሟያ ፈተና:- በተለዋጭ ፈተናዎች (AP/IB) ላይ የማለፊያ ውጤት የሚያገኙ ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ይዘት MCA መስፈርት ያሟላሉ።
[2]ክሬዲት ማዛወር:- ከሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ውጪ ቀይረው የሚመጡ ተማሪዎች አንዳንድ MCA ትምህርት መስፈርቶችን በዝውውር ክሬዲት ለማሟላት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

0617.24 • EGPS